# የሁሉም ነገር መታደስ



# የሁሉም ነገር መታደስ

WGS ሚኒስቴር

ፖ.ሣ.ቁ 90047

ሳን አንቶኒዮ, ቲ ኤክስ 78209

www.WGSministries.org

የቅጂ መብት © 2018 ጆናታን ዊሊያምስ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

ISBN-10:1985158922

ISBN-13: 978-1985158924

# ለምን?

ለምድንድን ነው ይሄ ሁሉ ምሬት ፣ ይሄ ሁሉ ሀዘን በዚህ ምድር ላይ ያለው?

ጉስቁልና፣ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር ፣ ጦርነት ፣ ባርነት ፣ ሰው ሰራሽ ረሀብ ለራሳቸው ስልጣን ብቻ በሚጨነቁ ፍትህ አልባ ምድር ላይ ሰው ሁሉ በአመፅ በአደጋ ውስጥ የሚኖረው? ይሄ ሁሉ አለምን እየረበሻት ነው፡፡



ጤና ማጣት፣ ሱስ፣ የተበተነ ቤተሰብ፣ የዘፈቀደ አመጽ ፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሱናሚ፣ የተፈጥሮ አደጋ፡፡ ሀዘን፣ እንባ፣ እና ታላቅ እልቂት፡፡ እያንዳንዱ ሰው በነዚህ ነገሮች ተነኪቷል፡፡ ከዚህ ሁሉ የልብ ስብራት ማንም አላመለጠም፡፡

## እነዚህን ነገሮች አስብ

- በዚህ ምድር መከፋትና ሀዘን ያለው ለም ይመስልሀል?
- አንተ በምትኖርበት ቤተሰብ ወይም መህበረሰብ ውስጥ ምን አይነት ችግሮች አሉ?
- በህይወትህ እያጋጠመህ ያለ ሀዘን፣ መከፋት ወይም ችግር አለ?

# ይሄ ሁል ጊዜ በዚህ መንገድ  አልነበረም

ለሰዎች ሁሉ ቅዱስ ቃል የሆነው መጽሀፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ በዚህ መንገድ እንዳለነበረ ይነግረናል፡፡ በመጀመሪያ ፈጣሪ ሰማያትንና ምድርን ሰራ፡፡ የሰራቸው ነገሮች ሁሉ መልካምና ውብ ነበሩ፡፡



በዚህ በእርሱ የፍጥረቱ ከፍታ ላይ የመጀመሪያው ወንድን የመጀመሪያዋ ሴት ቆሙ፡፡

## ከዘፍጥረት 1 እና 2 የፍጥረትን ታሪክ አንብብና ስለነዚህ ነገሮች አስብ

- በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ እግዚአብሄር ምን ተማርክ?
- እግዚአብሄር ለምንድን ነው የሰውን ዘር የፈጠረው?
- እግዚአብሄር አንተን ለምን የፈጠረህ የመስልሀል?

# ታላቁ ጥፋት

የእግዚአብሄር ቅዱስ ቃል የሆነው መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የመጀመሪያው ወንድና ሴት የእርሱ ልጆች በመሆናቸው አልረኩም ነበር፡፡ እግዚአብሄር እግዚአብሄር እንዲሆንና እርሱን በማምለክና በማገልገል አልረኩም ነበር፡፡ ስልጣንን ሁሉ ለራሳቸው ፈለጉ፡፡ ሊታሰብ በማይችል አመፅ ከዚህ አለም ፈጣሪ ራሳቸው በመለየት አወጁ፡፡



## ስለ ታላቁ ጥፋት ከዘፍጥረት 3 አንብብና እነዚህን ነገሮች አስብ

- በዚህ ታሪክ እባቡ ማን ነው?
- ሰውየውና ሴትየዋ ለምን እግዚአብሄርን ያልታዘዙት ይመስልሀል?
- ሰውየውና ሴትየዋ ባልታዘዙ ጊዜ ምን ሆነ?

# የሞት አራቱ አቅጣጫዎች

መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የሰው ሀጢያት ሀዘንን፣ ምሬትን እና ታላቁ ጥፋት ሞትን ወደ አለም እንዳመጣ ነው፡፡ ሞት የመጣው በአራት አቅጣጫዎች ነበር፡፡

## ሞቱ ወደ ላይ ነበር

የሰው ዘር በፈጣሪ ላይ አመፀ ከዚህ በኋላ እርሱን አላመኑበትም ወይም አላወቁትም ነበር፡፡ የራሳቸውን ምናባዊ አማልክትን ማለትም የእንጨትና የድንጋይ አማልክትን ማለትም መናገር ወይም መስማት ወይም ማየት የማይችሉ አማልክት ቀባዣሪ እና ጨካኝ አማልክትን መስራት ጀመሩ፡፡



## ሞቱ ውስጣዊ ነበር

ሰዎች ሰዎችን ማንሳቀል፣



ማግለል፣ ባሪያ ማድረግ እና መግደል ጀመሩ፡፡ ሀገራት በሀገራት ላይ ጦርነት አወጁ ፍትህ ወደ መሬት ተወረወረ፡፡ ሰዎችም በአለም ውሰጥ ስላለው ሀዘን አለቀሱና እንዲህ ብለው አሰቡ “የሆነ ተስፋ ይኖር ይሆን”?

## ሞቱ ወደ ታች ነበር

ምድር ከዚህ በኋላ የደስታ ገነት አልሆነችም፡፡ ከእግራቸው በታች የነበረችው ምድር የተረገመች ነበረች፡፡ እሾህና አረም አበቀለች፡፡ ምድር ሚዛኗን አጥታ ነበር፡፡ ድርቅ፣ ረሀብ፣ ጎርፍ፣ ቸነፈር፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፡፡ አለምን ህጻን ለመውለድ ምጥ እንደያዛት ሴት አስጨንቀዋታል፡፡



## ሞቱ ውስጣዊ ነበር

ሀፍረት፣ የጥፋተኝነት ስሜት፣ ብቸኝነት፣ ጭንቀት፣ ተስፋ መቁረጥና ፍርሀት የሰዎች ልብ ሞልቶት ነበር፡፡

### እነዚህን ነገሮች አስብ

- በአንተ ህዝብ፣ ቤተሰብ ወይም ህይወት ከእግዚአብሄር ጋር የነበረው ግንኙነት እንዴት ተበላሸ (ተናወጠ)?
- ከሌሎች ጋር የነበረህ ማንኛውም ግንኙነት እንዴት ተጎዳ?
- አንተ በምትኖርበት ምድር ህይወትን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምን አይነት ችግሮች አሉ?
- ከእነዚህ ችግሮች የትኞቹ በህይወትህ ያሉ ይመስልሀል?

| | |
|---|---|
| ☐ ሀፍረት | ☐ ፍርሃት |
| ☐ ጥፋተኝነት | ☐ ተስፋ መቁረጥ |
| ☐ ብቸኝነት | ☐ ጭንቀት |

# አለምን ለማዳንና ለማደስ የፈጣሪ እቅድ

ምንም እንኳን አለም ከእግዚአብሄር ፊትዋን ብትመልስም፤ እግዚአብሄር ግን አሁንም አለምን ይወዳል፡፡ እርሱ የፈጠራቸውንም ስለወደደ አለምንና የሰውን ዘር ወደ መጀመሪያው የፍቅርና የውበት እቅድ ለማደስ የሚጠቀምበትን አንድ ሰው መፈለግ ጀመረ፡፡

እናም አንድ ቀን እግዚአብሐሄር ያንን ሰው አገኘው፡፡ ስሙም አብርሀም ነበር፡፡



አብርሀም እውነትን የሚፈልግ ሰው ነበር፤ እናም በሚያየው ነገር በልቡ ይጨነቅ ነበር፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሄር አብርሀምን ተናገረው "አብርሀም፤ አብርሀም! ፍለጋህን አይቻለሁ፡፡ ልብህን ተመልክቻለሁ፡፡ እናም ወደ አንተ መጥቻለሁ፡፡ እኔ የፍጥረት ሁሉ እውነተኛ አምላክ ነኝ ሀገርህን፣ጎረቤቶችህንና ቤተሰቦችህን ትተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ሂድ ፡፡ ታላቅ ህዝብ አደርግሀለሁ፡፡ እባርክሀለሁ ታላቅም አደርግሀለሁ አንተም ለሌሎች በረከት ትሆናለህ በአንተም የምድርን ቤተሰቦች ሁሉ እባርካለሁ፡፡"



ይህ አብዮታዊ ነበር፡፡ ይህ ሀይለኛ ነበር፡፡ ይህ የተለየ ነበር፡፡

የትኛውም አማልክት እንደዚህ አይነት ነገር በዚህ አለም ላይ ተናገረው አያውቅም ነበር ምክንያቱም ደግሞ የዚህ አለም ጣኦታት እውነተኞች ስላልሆኑ ነው፡፡

ነገር ግን እውነተኛው አምላክ፣ ፈጣሪ፣ የሰውን ፍጥረት ወደራሱ መመለስ የሚፈልግ የፍቅር አምላክ  የተስፋንና የኪዳንን ቃል ይናገራል፡፡

## ለአብርሀም የመጣውን የእግዚአብሄር ቃል ከዘፍጥረት 12፡ 1-3 አንብብና እነዚህን ነገሮች አስብ

- እግዚአብሄር ለአብርሀም ምን ነገረው?
- በቁጥር 3 ላይ እግዚአብሄር ለአብርሀም የተናገረው አስፈላጊው ነገር ምን ነበር?
- እግዚአብሄር እነዚህን ተስፋዎች ለምን የገባ ይመስልሀል?

# ስለ አለም አዳኙ ተስፋዎች

በአጠቃላይ የአብርሃም ቤተሰብ እያደገ ሄደ እናም ታላቅ ህዝብ ሆነ፡፡ አንድ ቀን ለዚህ ህዝብ መሪ ይህ እውነተኛ አምላክ እንዲህ ብሎ ተናገረው "ለአብርሀም የተናገርኩትን ተስፋ እፈጽማለሁ፤ በዚህ ምድር ላይ ያለውን ሀዘንና ምሬት ሁሉ ወደ ፍጻሜ የሚያመጣውን ወደ አለም አመጣዋለሁ፡፡"

ይህ ድህነት እንዴት እንደሚደረግ በእስራኤል ነብያት በኩል ገልጿል፡፡ የሚመጣው ልዩ በሆነ ልጅ ነበር፡፡



*ህጻን ተወልዶልንልና*

*ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልንና፣*

*አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፡፡ ስሙም ድንቅ፣ መካር፣ ሀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡*

*ለመንግስቱ እና ለሰላሙ ፍጻሜ የለውም፡፡ ለዘለአለም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ በፍርድና በጽድቅ ይገዛል፡፡ የእግዚአብሄር ቅንአት ይህና አድርጓልና!*

# ተስፋ የተገባለት መወለድ

እናም አንድ ቀን ይህ ህጻን ተወለደ፡፡ የተወለደው እንደሌሎች ህጻን አልነበረም፡፡ የተአምራት ልጅ ነበር፡፡ ለሚሰሙትም ከሀጢያታቸው ለሚመለሱ ሁሉ ድህነት በማምጣት ይህን አለም ከምሬትና ከመከራ እንደሚያድን የእግዚአብሄር ልዩ ልጅ ምልክት ይሆን ዘንድ የተወለደው ከድንግል ነበር፡፡

ሲወለድ መላእክቶች ተገልጠው ነበር፡፡ ሰዎች እርሱን ለማምለክ ከሩቅ ቦታ መጥተው ነበር፡፡ ይህን ህፃን ስለሚሰራው ታላቅ ስራ የጥበብ ሰዎች ትንቢት ተናግረው ነበር፡፡ ይሄኛው የአለም አዳኝ ነበር ስሙም ኢየሱስ ነበር፡፡



## ከሉቃስ ወንጌል 2: 1-20 ስለ ኢየሱስ መወለድ አንብብና እስቲ እነዚህን ነገሮች አስብ

- ኢየሱስ ከድንግል የተወለደው ለምን ይመስልሃል?
- መላእክት ስለዚህ ልጅ ምን አሉ?
- ይህ ልጅ ማን ነበር እና ለምንስ ነበር ወደዚህ  ዓለም የመጣው?

# ተስፋ የተገባለት ህይወት

ኢየሱስ 30 አመት በሞላው ጊዜ አለምን የማደስ ተልእኮውን ለመጀመር ጊዜው እንደነበር አውቆ ነበር፡፡

የእግዚአብሄር መንግስት እንደቀረበችና ጊዜው እንደተፈጸመ በወገኖቹ መካከል እየተመላለሰ ያውጅ ነበር፡፡

ምድር የዚህ አለም መንግስታትን ጨለማና መከራ አይታ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ተራው የእግዚአብሔር መንግስት ወደ ምድር የሚመለስበትና ለምድር ድህነት የሚመለስበት ጊዜ ነበር፡፡



በኃይል ይናገር ነበር፡፡ በስልጣን ይናገር ነበር፡፡ በርህራሄ ይናገር ነበር፡፡ በሽተኞችን ፈውሷል፡፡ ሽባው እንዲራመድ አድርጓል፣ ሞተው የነበሩ ልጆች ያዝኑ ለነበሩ ቤተሰቦቻቸው ተመልሰው ተሰጥተዋል፡፡

በክፉ መንፈስ ተጠቅተው የነበሩ ነፃ ወጥተዋል፡፡ ከሁሉ በላይ በኃጢያታቸው አዝነው ወደ እርሡ የመጡትን ይቅር ብሏቸው ነበር፡፡ ተስፋንና አዲስን ጅማሬ ሰጥቷቸው ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ብርሀን ጨለማውን ሲገፍ ደስታ በምድር ላይ ተትረፍርፎ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ለገባው ቃል ኪዳን ታማኝ ነበር!

# ስለኢየሱስ ህይወት የሚናገሩትን ታሪኮች አንብብና እነዚህን ነገሮች አስብ

- ከሉቃስ 5፡12-16 ኢየሱስ በበሽታ ላይ ስላለው ስልጣን አንብብ
  ይህ ታሪክ ስለምን ያስተምርሀል? ይሄን ታሪክ መስማት ያለበት የምታውቀው ሰው አለ?

- ከሉቃስ 4፡31-37 ኢየሱስ በክፉ ላይ ስላለው ስልጣን አንብብ
  ይህ ታሪክ ስለምን ያስተምርሀል? ይሄን ታሪክ መስማት ያለበት የምታውቀው ሰው አለ?

- ከሉቃስ 7፡11-17 ኢየሱስ በሞት ላይ ስለነበር ስልጣን አንብብ
  ይህ ታሪክ ስለምን ያስተምርሀል? ይሄን ታሪክ መስማት ያለበት የምታውቀው ሰው አለ?

- ኢየሱስ ይቅር ለማለት ስላለው ስልጣን አንብብ በሉቃስ 5፡17-26
  ይህ ታሪክ ስለምን ያስተምርሀል? ይሄን ታሪክ መስማት ያለበት የምታውቀው ሰው አለ?

# የኢየሱስ ሞት

ሁሉም ሰው በኢየሱስ ደስተኛ አልነበረም፡፡ ኃይል አሁንም በክፉ ሰዎች እጅ ነው፤ ብዙ ጊዜ ከታላቁ ጥፋት ጊዜ ጀምሮ እነደነበርው ኢየሱስ ለሥልጣናቸው አስጊ ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡



ክፉ ሰዎች አድብተው ቀርበው አሰሩት፣ በቁጥጥር ስር አውለው፣ ለፍርድ በማቅረብ፣ ባልፈፀመው ወንጀል በመክሰስ በሮማውያን መስቀል ላይ ሰቀሉት፡፡

## ከሉቃስ 22: 54-23 : 56 ስለ ኢየሱስ ሞት አንብብና እስቲ እነዚህን ነገሮች አስብ

- መሪዎቹ እርሱን ይቃወሙት የነበረው ለምንድን ነው?
- ኢየሱስ "አባት ሆይ, የሚያደርጉትን እያውቁምና ይቅር በላቸው" ያለው ለምን ይመስልሃል? ኢየሱስ በደል የፈጸሙትን ሰዎች ይቅር እንደሚላቸው ማወቅህ አንተ ምን እንዲሰማህ ያደርጋል?
- በዚያው ዕለት ሌላ ሰው ከኢየሱስ ጋር ሞቷል፡፡ ያ ሰው ኢየሱስን ምህረትን የጠየቀው ሲሆን ኢየሱስም በገነት ከእርሱ ጋር እንደሚኖር ተናግሯል፡፡ ይህስ ስለ ኢየሱስ ምን ያስተምረናል?

# የኢየሱስ ትንሳኤ

በመጨረሻም ጨለማ ያሸነፈ ይመስል ነበር፡፡ በሦስተኛው ቀን አንድ ነገር እስኪሆን ድረስ ወደ አለም የመጣው ብርሃን ድል የነተሣ ይመስል ነበር፡፡

ሴቶቹ የኢየሱስን አካል ዘይት ሊቀቡ ወደ መቃብሩ ሄዱ ነገር ግን እዚያ ሲደርሱ መቃብሩ ባዶ ነበር፡፡ መላዕክቱም ተገለጡላቸውና ታላቁን ዜና አወጁላቸው፡፡



*ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል! ኢየሱስ ከሙታን ተነስቶ ነበር ከዚህም በኋላ የማይሞትን አካል ለብሦ ነበር፡፡*

*ኢየሱስ በጨለማ አልተሸነፈም ነበር፡፡ በምትኩ ኢየሱስ ጨለማን አሸንፎ ነበር፡፡*

የመስቀል ላይ የሞቱ ሽንፈት
አልነበረም፡፡ ለአለም ሀየጢያት በመስቀል ላይ የከፈለው እርሱ ድል እንጂ ፡፡

በእርሱም ትንሣኤ ለአብርሃም በገባው ቃል መሰረት ሁሉን ነገር የሚያድስበትን አዲሱን የእግዚአብሔር ፍጥረት አስተዋውቆ ነበር፡፡

# ከሉቃስ 24፡ 1-43 ስለ ኢየሱስ ትንሳኤ አንብብና እስቲ እነዚህን ነገሮች አስብ

- ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ መጀመሪያ ለማን ተገለጠ?
- ኢየሱስ ወደ ኤማሁስ መንደር ሲጓዙ ለነበሩት ሁለት ሰዎች እየተናገረ ሳለ ምን እያስተማራቸው ነበር?
- ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥ በፊታቸው ምግብ የበላው ለምን ይመስልሃል?
- ከሙታን የተነሳው ኢየሱስ "ሰላም ለእናንተ ይሁን!" አለ፡፡ ኢየሱስ በአንተ ህይወት ላይ ሰላም መናገር የሚፈልግ የመስልህል?
- ከሞት ስለተነሳው ኢየሱስን እና ስለ እርሱ ሰላም ሌላ ማን መስማት ያለበት ይመስልሀል?

# የኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ለአንተ፣ ለቤተሰብህ እና ለአገርህ ምን ማለት ነው?

## የኢየሱስ ሞት

የእግዚአብሄር ቅዱስ ቃል  የኢየሱስን ሞት በአጋጣሚ የሆነ ወይም አሳዛኝ ታሪክ እንዳልሆነ ያስተምረናል፡፡ የእርሱ ሞት እኛ ይቅር መባልን እንድናገኝ እግዚአብሄር ለሀጢያታችን መሰዋእትነት ያዘጋጀው ዕቅድ እንደሆነ ያስተምረናል፡፡

ከእግዚአብሔር  ቃል እነዚህን ሁለት ንግግሮች አንብብ፡፡

*"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።"*

- ሮሜ 3:23

*"የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና; የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።"* - ሮሜ 6:23

የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ሁላችንም ኃጢአት እነደሰራንና ከእግዚአብሔርም ፊታችንን እንዳዞርን ያስተምረናል፡፡ የእኛ ኃጢአት ከእግዚአብሔር እንደለየንና ሞት ወደ ዓለም እንዲመጣ እንዳደረገ ያስተምረናል፡፡  ነገር ግን ኢየሱስ ለኃጢአታችን ቅጣቱን እንደከፈለልን እና በእርሱ በኩል ይቅርታን እና ሕይወትን እንደምናገኝ ያስተምረናል፡፡

ኢየሱስ በእኛ ምትክ ስለ መሞቱ የሚያብራራውን ይህንን መግለጫ ያንብቡ፡

*"ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሄርእንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንዲ ጊዜ በሀጥያት ምክንያት ሞቶአልና፡፡"* - 1 ጴጥሮስ 3:18

ኢየሱስ የአንተን ሐጢያት  በራሱ ላይ ወስዶ የአንተን ቤተሰቦች፣ የአንተን የህዝቦችና እና የዓለምን የኃጢአት ዋጋ  ከፍሎዋል-!

ልታስብበት የሚገባው ጥያቄ ይህ ነው፡



ኢየሱስ ለኃጢያተኛው ዓለም፣ ለቤተሰብህ እና ለአንተ እንዴት እንደሞተ ስትመለከት ይህ እንዴት እንዲሰማህት ያደርጋል?

## የኢየሱስ ትንሳኤ

ኢየሱስ ከሶስት ቀናት በኋላ ከሞት ሲነሳ በመስቀል ላይ መሞቱ እኛን ወደ እግዚአብሄር ለመመለስና ሀጢያታችንን ለመክፈል በቂ ነበር፡፡ ለኃጢያታችን ክፍያ ተከፍሏል! ይቅር ልንባልና እና ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ እንችላለን!

ኢየሱስ ከሶስት ቀናት በኋላ ከሞት ሲነሳ፣ ስለ እርሱ ማንነት ይህም እርሱ ለሰው ሁሉ መድሃኒት እና እውነተኛ አዳኝ እንዲሆን ወደአለም እንደሚመጣ ተስፋ የተሰጠውና እየተነገረ የነበረው ነገር ሁሉ እውነተኛ እንደሆነ ለአለም አሳይቷል!

የእግዚአብሔር ቅዱስመጽሐፍ ይህንን ተስፋ ይሰጣል፣

*"ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሞት እንዳስነሳው ብታምን ትድናለህና፤ የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና፡፡"*

– ሮሜ 10: 9, 13

ኢየሱስን እንደ አዳኝህና ጌታህ እንዲሆን ትፈልጋለህ? ኢየሱስ ሕያው ነው፡፡ ይወድሃል፡፡ ለኃጢአታችሁ ሞቷል፡፡ ህይወትህን ለመባረክ ከሞት ተነስቷል፡፡ እሱ እንደነዚህ ያሉ ቃላትን በመጠቀም እንድትጠይቀው እየጠበቀህ ነው፡፡



"ውድ ጌታ ኢየሱስ፣ ወደ ዓለም ስለመጣህ አመሰግናለሁ፡፡ ለሰዎች ስላለህ ፍቅር እናመሰግንሀለሁ፡፡ የታመሙትን ፈውስሃል፡፡ ሰዎችን ከክፉ መናፍስት ነጻ አውጥተሀል፡፡ ሙታንን አስነስተሀል፡፡. ለኃጢአተኛ ሰዎች ርኅራኄ አሳይተሃል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ስለኔ ኃጢአት እንደሞትክ ገብቶኛል፡፡ እባክህ ላደረግኩት ሁሉ ይቅርታ አድርግልኝ፡፡ ወደ ህይወቴ እንድትመጣ እና አዳኝ እና ጌታ እንድትሆነኝ እፈልጋለሁ፡፡ እኔ አንተን መከተል እና ስለአንተም ሌሎችን መናገር እፈልጋለሁ! አሜን! "

# ኢየሱስ ከተነሳ በኋላ

ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ተከታዮችን ሰብስቦ በእጆቹ እና በእግሮቹ ላይ ያሉትን በእንጨት ላይ የተቸነከረውን ጠባሳዎች አሳያቸው፡፡

እርሱ በመስቀል ላይ ሲሞት በእርሱ ላይ የተደረገበት ፍትህ አልባ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ሀይል ለሠዎች ድህነት እንዲሆን እንደለወጠው ገልፆላቸው ነበር፡፡



በመስቀል ላይ ሲሞት ለአለም ሀጢያት እርሱ ቅጣቱን ከፍሏል፡፡ የሠው ዘር በአመፁ ምክንያት ጥፋተኛ ሆኖ እና ተረግሞ ነበር፡፡ ፍርዱ የሚገባው ለሰው ዘር ነበር ነገር ግን ኢየሱስ የሁሉንም ቅጣት እርሡ ወሰደው፡፡ አሁን ሠዎች ሐጢያታቸው ይቅር ተብሎ ወደ ፈጣሪያቸው ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

እውነተኛውና ፍፁም ሆኖ ራሱ ኢየሱስ መስወአት ሆኖ ስለቀረበ ከዚህ በኋላ ሠዎች ለሠሩት ሀጢያት የእንስሳት መስወአት አያቀርቡም፡፡ ኢየሱስ ሞትን ከሞት በመነሳት ስላሸነፈው ከዚህ በኋላ ከሞት በኋላ ፍርሃት የለም፡፡

በሽተኞችን ይፈውስ የነበረውና ሀጢያትን ይቅር ያለው እውነተኛ ጌታ ሆኖ ጠላትን ሁሉ አሸንፎ ከሞት ተነስቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ተከታዮቹን ወደ አገልግሎት ሊልካቸው እንደሆነ ነገራቸው፡፡ ተልኳቸውም የነበረው ለአለም ስለ እርሱ እንዲናገሩና ለሰዎች፣ ለቤተሰቦቻቸውና ለመህበረሰቡ ተህድሶን እንዲያመጡ ነበር፡፡

ተልዕኳቸውም የነበረው ሐጢያታቸው በእርሡ ይቅር እንደሚባል፣ በታላቁ ጥፋት ጠፍተው የነበሩት ሁሉ እነዚያ ህይወቶች በእርሡ እንደሚገኙና አሁን በእርሡ ሊታደሱ እንደሚችሉ ለአለም መንገር ነበር፡፡

ሰዎች እውነተኛውን አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሲያገኙ በሠውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ጨለማ ይነሳል፡፡



ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ እንዳስተማረው አንዳቸው ሌላውን ሲያገለግሉ በሰዎችና በሰዎች መካከል ያለው ጨለማ ይነሣል፡፡

በእያንዳንዱ ሠው ውስጥም ያለው ጨለማ የኢየሱስ መንፈስ መጥቶ ሲያነፃን፣ ሲፈውሰንና ሲያድሰን ሊነሳ ይችላል፡፡

በፍጥረትም ላይ ያለው መርገም ኢየሱስ ሰላምና ደስታ ያለባትን ውብ አለም ለመስራት ዳግመኛ አንድ ቀን ሲመጣ ያኔ ይነሣል፡፡

# ኢየሱስ ለአንተ ምን ይፈልጋል?

ኢየሱስ እንድታድግ እና ጠንካራ የበሰለ የእርሱ ተከታይ እንድትሆን ይፈልጋል፡፡ ኢየሱስን ወደ ህይወትህ እንዲመጣ በጠየከው ጊዜ መጥቷል አሁን ሙሉ በሙለ በመንፈስ ሊሞላህና እና በሁሉም አቅጣጫ ህይወትህን ሊለውጠው ይፈልጋል፡፡ ከኢየሱስ ጋር ባለህ ግንኙነት ለማደግ ልታደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡

1. **የኢየሱስ ተከታይ የሆነ ሰው ያጠምቅህ፡፡** የውኃ ጥምቀት ከሞት ወደ ህይወት መሸጋገርህንና አሁን የኢየሱስ ተከታይ መሆንህን የሚያሳይ ምልክት ነው፡፡ ጥምቀት በመስቀል ላይ መሞቱ ለአንተ እንደነበረ እና ከሞት መነሳቱ ሕይወትን ሊሰጥህ እንደሁነ ማሳያ የእምነት እርምጃ ነው፡፡ . ኢየሱስ "ሂዱና በአብ፣ በመልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ " ብሏል.- ማቴዎስ 28: 18-20



2. **ኢየሱስን** እንዲለውጥህ፣ እንዲቀይርህና ለሌሎች ሰዎች ምስክር ትሆን ዘንድ **በመንፈስ ሙሉ በሙሉ እንዲሞላህ ጠይቀው፡፡** ከኢየሱስ ተከታዮች መካከል አንዱ የነበረው ጳውሎስ "በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞሉ፣ እርስ በርሳችሁ መልካም ነገር ተነጋገሩ፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፣ እንዲሁም ከሌሎች ጋር በትህትና ኑሩ፡፡ " ብሏል፡፡

3. **በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ቃል ተማር**
   - ስለ ኢየሱስ ሕይወት ከማቴዎስ፣ ከማርቆስ፣ ከሉቃስና ከዮሐንስወንጌላት ተማር፡፡
   - በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስለ ኢየሱስ የመጀመሪያ ተከታዮች ተማር፡፡

- የኢየሱስ ተከታዮች ችግሮቻቸውን እንዲቋቋሙ እና በእምነታቸው እንዲያድጉ ለመርዳት የኢየሱስ ተከታዮች ከጻፏቸው መልእክቶች ተማር፡፡
- ኢየሱስ እንዴት ጌታ እንደሆነና እያንዳንዱን ችግር እንደሚያሸንፍና ሁሉም ነገር እንደሚያድስ ከራዕይ መፅሀፍ ተማር፡፡

4. **በየቀኑ ስለ ሁሉም ነገር ወደ እግዚአብሔር ጸልይ!** እግዚአብሔር እንደ ልጁ ይወድሀል፡፡ እርሱ ሁሉንም ስጋቶችህን፣ ፍላጎቶችህን እና ሁሉም ምኞቶችህን ወደ እርሱ እንድታመጣው ይፈልጋል፡፡

*"ጌታ ቅርብ ነው፡፡ በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሄር ዘንደ ልመናችሁን አስታውቁ እነጂ በአንዳች አተጨነቁ አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሄር ሰላም ልባችሁንና ሀሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ የጠብቃል ፡፡ "* - ፊልጵስዩስ 4: 6-7



5. **ከሌሎች ከኢየሱስ ተከታዮች ጋር ዘወትር ተገናኝ፡፡**
ለማደግ፣ እንዲጸልዩልን፣ እንዲንከባከቡን፣ እንዲመሩን፣ እንዲወዱን እና እንዲረዱን ሌሎች አማኞች ያስፈልጉናል፡፡ እኛም እንደዚያው ማድረግ እንችላለን፡፡

*"ለፍቅር እና ለመልካምም ስራ እንድንነቃቃ እርስበርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው መሰብሰባችንን አንተው፡፡"* - ዕብራውያን 10: 24-25

## 6. ለሌሎች ፀልይ እንዲሁም ከኢየሱስ ጋር ያለህን ግንኙነት ንገራቸው፡፡

ኢየሱስም እንዲህ አለ:


*"ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሳል በስሙም ንስሀ እና የሀጢያት ስርየት ከኢየሩሳላም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ የሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፏል፡፡ እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ፡፡*

- ከሉቃስ 24: 46-48



# ኢየሱስ እውነተኛው የአለም ጌታ እና የአንተ ጌታ

ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኃላ ተከታዮቹን ሰብስቦ እርሱ የመጣው ሁሉም ሰው እንዲታደስ እና ወደ ፍጣሪው ለመመለስ መሆኑን ለመላው አለም እንዲነግሩ ይህን ተልዕኮ ሰጣቸው፡፡




ከዚያም የሰማይና የምድር ጌታ ሆኖ በዙፋን ወደ ተቀመጠትን ወደ ሰማያዊ ቦታው ተመለሰ፡፡ አሁን እንደ እውነተኛው ዓለም ጌታ ፣ የሰው ዘር አዳኝ በታላቁ ጥፋት ወቅት ያጣናቸውን ነገሮች በሙሉ ወደ ነበሩበት ይመልሳል በማለት ተከታዮቹን ይህን የሚያስደስት ዜና እነዲያሰራጩ ያስታጥቃቸዋል፡፡

አዎ! እግዚአብሔር ዓለም በሙሉ በጨለማ ውስጥ ከመሆኑ ቀደም ብሎ ለአብርሃም ለገባለት ቃል ኪዳን ታማኝ ነበር፡፡ በአብርሃም የዘር ሐረግ የናዝሬቱ ኢየሱስን ልኮ እርሱ እንደተናገረው ዓለምን እየባረከ ነው፡፡ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ይህን የተስፋ ቃል፣ ደስታና ሕይወት እየተቀበሉ ሲሆን እነሱም ደግሞ ለሌሎች ያስተዋውቁ ነው፡፡



ይህ የእግዚአብሔር የድህነት መልእክት አለምን መዞር ከጀመረ 2000 አመታት አለፉ፡፡ አሁንም በመላው ዓለም እየተሰራጨ ሲሆን ዛሬ ደግሞ ይህ መልዕክት ወደ አንተ መጥቷል፡፡



ከፍርሀቶችህ ነፃ ትወጣለህ፡፡

ኃፍረትህ ይወገዳል፡፡

ሀጢያትህ ይቅር ሊባል ይችላል፡፡

ተስፋ መቁረጥህም ይጠፋል፡፡

ግጭቶችህም በአዳኙና በሠማይመና በምድር ፍፁም ለሀጢያታችን



በተሰዋው ሞትን ባሸነፈው የሁሉ ጌታ በሆነው በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም ይፈታሉ፡፡



ዛሬ ጌታ አድርገህ ተቀበለዉ! አሁን እርሡን ጥራውና ጌታህ እንደሆነ ተናገር እንዲሁም ለሌሎችም ይህንን አስደሳች ዜና ንገር!

## ስለ ሁሉም ነገሮች መታደስ የሚገልጸው ይህ አስደሳች ዜና ወደ የቀረበልህ በWGS ሚኒስቴር

ፖ.ሣ.ቁ 90047
ሳን አንቶኒዮ, ቲ ኤክስ 78209
አሜሪካ

1.210.717.6617
info@WGSministries.org

www.WGSministries.org

የሁሉም ነገር መታደስ ከዚህ በታች  ይመልከቱ
www.WGSministries.org/renewal-video/

Exponential Gospel Mission
INTERNATIONAL

**PR. MEZGEBU** TSEMRU, Director

+251 91 162 1558

Mezgebu105@yahoo.com

Photos on pages 1,5,22,24 courtesy of Creative Commons